ሞንትጎመሪ ካውንቲ ምክር ቤት

ከምክር ቤት አባል ኤቫን ግላስ ቢሮ *ማርች 18, 2020*

ለማናገር፣ ቫለሪያ ካራንዝ 240-777-7954

የ ዜ ና መ ል ዕ ክ ት

ምክር ቤቱ ለባንኮች፣ የገንዘብ ተቋማት እና የህዝብ ዩቲሊቲዎች ክፍያ ላልፈጸሙ ደንበኞች ለ 60-ቀናት የሚቆይ እግድ እንዲያደርጉ ጥሪ ያቀርባል

ሮክቪል፣ ኤምዲ፣ ማርች 18, 2020 — ለኖቬል ኮሮናቫይረስ ወረርሽኝ ምላሻችንን በምንመራበት ወቅት የህዝብ ጤና እና የሁሉም ነዋሪዎች ደህንነት የምክር ቤቱ ዋናው ቅድሚያ የምንሰጠው አንው። ምክር ቤቱ የተፈጠሩትን ከባድ የገንዘብ ጉዳቶችን በነዋሪዎቻችን፣ በንግድ ቤቶች ባለቤቶች፣ እና በትርፍአልባ ድርጅቶች ላይ ያለውን እና የሚቀጥለውን ጫና ይረዳል። የሞንትጎመሪ ካውንቲ ምክር ቤት ከካውንቲው ስራ አስፈጻሚ ማርክ ኤልሪች፣ ገቨርነር ላሪ ሆጋን እና የፌዴራል አጋሮቻችን ጋር በጋራ ለመስራት ዝግጁ ሲሆን አስፈላጊ ድጋፎችን ከስራ ለተቀነሱ ወይም የስራ ሰኣት ለተቀነሰባቸው ነዋሪዎች እንዲሁም በንግድ እጦት ወይም ቅነሳ ከባድ የኢኮኖሚ ችግር ላጋጠማቸው የትናንሽ ንግድ ተቋማት ያቀርባል።

በምክር ቤቱ በባንክ እና ዩቲሊቲ ድንጋጌ ላይ ባለው ውስን የህግ ስልጣን፣ ባንኮችን፣ የገንዘብ ተቋማትን እና የህዝብ ዩቲሊቲዎች የ 60-ቀናት የሚቆይ እግድ መክፈል ላቆሙ ደንበኞች በማድረግ በኮቪድ-19 ወረርሽኝ ምክኒያት ያጋጠማቸውን የገንዘብ ቀውስ ለማቃለል እንዲረዳ እየጠየቅን ነው።

ብዙ የህዝብ ዩቲሊቲዎች እያቀረቡ ያሉት የክፍያ ድጋፍ፣ የመዘግየት ክፍያዎች እና የጋዝ፣ ኤሌክትሪክ እና ውሃ አገልግሎቶች መቋረጥን ማቆየት ሲሆን፣ ምክር ቤቱ እነዚህን ክንውኖች ቢያንስ ለ 60 ቀናት እንዲቀጥሉ ያበረታታል። ምክር ቤቱ በተጨማሪም ባንኮች እና ሌሎች የገንዘብ ተቋማት የድንገተኛ ድጋፍ እቅድ እንዲያዘጋጁ፣ የክፍያ ማንሳትን፣ የብድር ማስተካከያዎችን፣ የክፍያ መጨረሻ ቀናት ማራዘምን፣ የደሞዝ ቅድሚያን፣ ዝቅተኛ ወለድን፣ እና ወለድ አልባ ብድርን፣ እንዲሁም ሌሎች የችግር ጊዜ ድጋፎችን እንዲያደርጉ ይጠይቃል።

“እንደ ቀድሞ የትንሽ ንግድ ቤት ባለቤት፣ በመልካም ጊዜያት እንኳን በቂ ንብረቶች ምን ያህል አስፈላጊ እንደሆኑ አውቃለሁ። በነዚህ አስቸጋሪ እና ያልተጠበቁ ጊዜያት፣ ይህ በጣም ወሳኝ ይሆናል።” ብለዋል **የምክር ቤቱ ፕሬዚደንት ሲድኒ ካተዝ**። “ከሲኦጂ (የመንግስታት ምክር ቤት)፣ እና ከመንግስታችን አጋሮች ጋር እነዚህን አስቸጋሪ ነገሮች ለማስተካከል በጋራ ለመስራት ቁርጠኛ ነኝ።”

“ሁላችንም በጋራ በመስራት ወዳጆቻችን እና ጎረቤቶቻችን በዚህ አስቸጋሪ ጊዜ ማገዝ አለብን። የምክር ቤት መንግስት ነዋሪዎቻችንን እና ትንሽ ንግድ ቤቶችን ለማገዝ የምንችለውን ሁሉ እናደርጋለን።” ብለዋል **የምክር ቤቱ ምክትል ፕሬዚደንት ቶም ሀከር**። “የፌዴራል መንግስት እና የግል አጋሮችን የዚህን ቀውስ የኢኮኖሚ ጉዳት ለመቀነስ ድንገተኛ እርምጃዎች እንዲወስዱ እየጠየቅን ነው።”

“በዚህ የጤና ቀውስ ወቅት እየሰራሁ ያለሁት ከትርፍ አልባ ማህበረሰባችን ጋር ሲሆን ይህም እነሱ እና የነሱ ብዙ ተጋላጭ ደንበኞቻቸው ያጋጠማቸውን ችግር ለማገዝ ነው። እነዚህ ድርጅቶች ስራቸውን መስራት እንዲቀጥሉ እና በገንዘብ እገዛ የሚሰሩትን መልካም ስራ እንዲቀጥሉ ማስቻል በጣም አስፈላጊ ነው።” ብለዋል **የምክር ቤቱ አባል ጌብ አልቦርኖዝ፣ የምክር ቤቱ ጤና እና የሰብአዊ አገልግሎቶች ሰብሳቢ**። “አጠቃላይ ማህበረሰባችን በጋራ በነዚህ ቀናት እና ሳምንታት በህብረት ለመቋቋም እንደሚችል ተስፋ አደርጋለሁ።”

“እነዚህ በጣም አስቸጋሪ ጊዜያት ናቸው። የሞንትጎመሪ ካውንቲ ነዋሪዎች ስለወዳጆቻቸው ጤና፣ ስለ ትናንሽ ንግድ ቤቶች ለሰራተኞቻቸው ደሞዝ መክፈል መቻል፣ እና ስለትርፍ አልባ ድርጅቶች የህብረተሰባችን የደህንነት መረብ ጥንካሬ በሰራተኞቻቸው ማረጋገጥ ስጋት አድሮባቸዋል።” ብለዋል **የምክር ቤቱ አባል ኢቫን ግላስ፣ የቤት አልባነት እና የተጋላጭ ማህበረሰቦች መሪ**። “ትናንሽ ንግድ ቤቶች፣ ትርፍ አልባ ድርጅቶች እና ነዋሪዎችን ለማገዝ የምንችለውን ሁሉ ማድረግ አለብን፤ ባንኮች እና የገንዘብ ተቋማት ይህንን በተመሳሳይ እንዲያደርጉ ጥሪ አቀርባለሁ። የገንዘብ ተቋሞቻችን የ 60-ቀን የብድር ክፍያ እግድ በማድረግ በግለሰቦች እና ንግድ ቤቶች ያጋጠማቸውን ጫና ለማቃለል ማድረግ አለባቸው። ሁላችንም በዚህ አንድ ላይ ነን።”

“ይህ ወቅት ማህበረሰባችን በጋራ መቆም ያለበት ወሳኝ ጊዜ ነው።” ብለዋል **የምክር ቤቱ አባል ሃንስ ራይመር፣ የምክር ቤቱ እቅድ፣ መኖሪያ ቤት፣ እና የኢኮኖሚ ማጎልበት ኮሚቴ ሰብሳቢ**። “የበሽታውን ስርጭት ለመቆጣጠር የምንችለውን ሁሉ ማድረግ ሲገባን፣ የአካባቢው ንግድ ቤቶች አደጋው ካለፈ በሁዋላ እንዲያገግሙ ለማድረግ ማገዝ አለብን። እንደ ባንክ ያሉ አበዳሪዎች እና አከራዮች ተለዋዋጭ እና ለዚህ ልዩ ሁኔታ ተመች በመሆን የሚጠበቅባቸውን እንዲወጡ ያስፈልጋል።”

“ይህ ቀውስ እንደ ተባበረ ማህበረሰብ በጋራ ለመቆም እና ለመደጋገፍ፣ በተለይ በመሃከላችን ተጋላጭ ለሆኑት፣ ልዩ እድል ይሰጠናል።” ብለዋል **የምክር ቤቱ አባል ናንሲ ናቫሮ፣ የምክር ቤቱ የመንግስት ስራዎች እና የገንዘብ ፖሊሲ ሰብሳቢ**። “ባለኝ ሃይል ሁሉ የሚያስፈልገውን ለማድረግ፣ ከስራ ባልደረቦቼ ጋር በመስራት፣ ለነዋሪዎቻችን ድጋፍ ለመጠየቅ ቃል ገብቻለሁ።”

“በነዚህ አገራችን ይህንን በሽታ በምትታገልበት ወሳኝ አሳሳቢ ቀናት፣ ይህንን ማእበል ለመቋቋም ያሉትን ሁሉ እድሎች እንዳላቸው ማረጋገጥ አለብን።” ብለዋል **የምክር ቤቱ አባል ክሬግ ራይስ፣ የካውንስሉ የትምህርት እና ባህል ሰብሳቢ**። “በዚህ የገንዘብ ቀውስ ወቅት የብድር እረፍት ማበረታታት መደረግ ያለበት ትክክለኛ ነገር ነው።”

“ይህ አንገብጋቢ ቀውስ የሚጠይቀው በፌዴራል፣ ስቴት፣ እና በአካባቢ ደረጃ አንገብጋቢ ምላሽ ይጠይቃል -- የአንገብጋቢ የህዝብ ጤና ድንገተኛ ቀውስ ለመታገል፣ እና ትልቁን የማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ጫናዎች በማስተካከል ስርጭቱን ለመቀነስ የሚያስፈልጉ እርምጃዎችን በመውሰድ መሆን አለበት።” ብለዋል **የምክር ቤቱ አባል አንድሪው ፍሪድሰን**።

“ነዋሪዎቻችን እና ትናንሽ ንግድ ቤቶቻችን በኮርቪድ 19 ቫይረስ የተነሳ ካሉት መዘጋቶች ለማገገም ጊዜ እና እርዳታ ይፈልጋሉ። በጋራ በመስራት ለአካባቢያችን ኢኮኖሚ ለመጠገን አንድ ላይ መተባበር አለብን።” ብለዋል **የምክር ቤቱ አባል ዊል ጃዋንዶ**።

# # #